# ዜሮ ለዜሮ
# መጨረሻው ዜሮ !

ከአዕምሩ
ሎስአንጀለስ

ተቀበል አዝማሪ ግጥም ልንገርህ
መሰንቆህን ቃኘው እስኪ በናትህ
ከሩቅ የመጣ ሰው ትመስለኛለህ
ረጅም ተጉዘህ ምንም ቢደክምህ
ትንሽ አንጎራጉር አዝማሪ አይደለህ?

ከሁሉ አስቀድሞ ሰላምታ ይበልጣል
ጤና ይስጥልኝ ጌታው እንደምን ውለዋል
አዝማሪ መሆኔን በምን አወቁኝ
ግጥምዎን ደርድው ዝፈን የሚሉኝ
እኔ እንደሆንኩ አዝማሪ ሲያልፍ የማይነካኝ
ልጅዎን ጥየቃ ነው የመጣሁኝ
እባክዎት ይስጡኝ ሚስት እንድትሆነኝ ?

ሰውየው ገርሟቸው ቁጭ ብድግ እያሉ
ጉድ በሉ አገሬ ጉድ በሉ
የድፍረቱ ድፍረት አይ አቀላለሉ
ደግሞ እንደጤነኛ ጭራ ማንጠልጠሉ
የውሸት ሳቅ ብለው ታች ከላይ አዩትና
እንኳንስ ጠይቆ እንዳንተ ያለ ጅና
ተለምኖ ይሰጣል ሴትን ልጅ ለጀግና
እልፍኙ አለችልህ ውሰዳት ግባና

አዝማሪው ደስ ብሎት ለሰውየው ስግዶ
እልፍኙን እያየ ተሻገረ ማዶ

እባክህ እንተየ እስኪ ልጠይቅህ
የኔን ልጅ ለማግባት ማነው ያማከረህ?
በርግጥም ነግረሽኛል አዝማሪም እንዳልሆንህ
ከየት አምጥተህ ነው መሰንቆ ማንገትህ
ወይስ ሰርቀሽው ነው፣ ተሸከመው ተብለህ
እውነቱን ንገረኝ አረ በፈጠረህ?

የመሰንቆውና የልጅዎ ነገር
ከባድ ነው ምስጢሩ ባንድ ጊዜ መናገር

ያውቋቸው ይሆን ሊቀ መኳስ ጉዱን
በስርግ በዝክሩ የሚወደሱትን
እሳቸው ነግረውኝ ሁሉንም በዝርዝር
የእርስዎን ሀብትና የልጅዎን ማማር
ይዘውኝ ሲመጡ ደረሰን እወንዝ ዳር
ከሩቅ በመጣ ጎርፍ መልካው ግጥም ብሎ
ድንጊያውና እንጨቱን ሲያጉዘው ነቃቅሎ
ወንዙ ገባ ብለው ሊቀ መኳስ ጅሎ
መሰንቆ እየመቱ ጀመሩ አይ ላሎ
እንኳንስ መሰንቆ ቢነፋም እንቢልታ
እየባሰ ሄደ የጎርፉ ድንፋታ
እኔም ነገርኳቸው አይገቡ ከወንዙ
መዝፈን ካማረዎ ጥገዎን ይያዙ
ጎርፍ የማይምር ነው ምንም ቢናዘዙ
ሳቅ ሳቅ እያሉ አደራ ነገሩኝ
በኔ ላይ ጨክኖ ጠርጎ ከወሰደኝ
ጭራየን አደራ እንድትይዝልኝ
ትንሽም ሳይቆዩ ይህን ተናግረውኝ
ፈረሰኛው መጥቶ ድንገት ወስደብኝ
አደራ ክፉ ነው ጭራ ይገፔ ቀረሁኝ
ጉዳዩ ይኸው ነው በውነት ካደመጡኝ

በል ሂድና ግባ ጫማህን አውልቀህ
እኔም መጣሁልህ መርቂ እንድሰጥህ
ቁጭ በል መደቡ ገላህንም ሰደህ
የምታምር ልጄን ከጓዳ ሳምጣልህ
ብለው ጎዳ ገብተው
የተወለወለ ሞይዘር አቀባብለው
ተመልሰው ወጡ ጭራ ካነገተው
የወዳጄን መሞት በድንገት መንገርህ
ልጄን እንዳጋብህ ደፍረህ መጠየቅህ
አታውቀኝ አላውቅህ
ምን አይነት ዓይን አውጣ ደፋርነህ እባክህ
በያዝኩት ጠብመንጃ አንድ ጊዜ ሳልግተህ
የያዝኸውን ጭራ ከእንግተህ አውልቀህ
ብታውቅም ባታውቅም በዕጣን አለስልስህ
ዘፈን ዝፈንልኝ በኃይል ጮህ ብለህ

ቱኒም ተደናግጦ ጀመረ እንጉርጉሮ
የማያውቅበትን የሰው ጭራ አክሮ
ጉዴ ነው ዘንድሮ
ሁሉም ዜሮ ዜሮ
ፀሀይቱም ዜሮ
ጨረቃዋም ዜሮ
እኔም ዜሮ ዜሮ
አዝማሪውም ዜሮ እንጀራውም ዜሮ
ብሎ አውደመው ጭራውን ሰባብሮ!